# ኢትዮጵያ እና ግብፅ፤ከሙርሲ እስከ ዓል.ሲሲ

**ሰለሞን ሽፈራው** 11-30-17

አሁን በስልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት ከቀደሙት ስርዓቶች የተለየ ተደርጎ የሚወሰድባቸው የራሱ የሆኑ ባህሪያት እንዳሉት የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም:: የፌደራላዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ መንግስትን ከዚህ ቀደም በሀገራችን ስልጣን ላይ ከነበሩት አሀዳዊ ስርዓተ መንግስታት የተለየ እንዲሆን ከሚያደርጉት የአጠቃላይ መንግስታዊ ቁመናው አንኳር-አንኳር መገለጫዎች መካከል አንዱ ደግሞ የሚከተለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነው ማለት ይቻላል። እናም የኢፌድሪ መንግስት ከትናንት እስከ ዛሬ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ስለሚታወቅበት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ልዩ ባህሪያት ሲነሳ በተለይም ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን አብሮ ማንሳት ግድ እንደሆነ ተደርጎ ይታመናል።

ከሁለቱ የኢፌድሪ መንግስት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መለያ ባህሪያት የመጀመሪያው መሠረታዊ ነጥብ፤ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ህዝቦች ሀገራዊ ደህንነትና ዘላቂ ጥቅም ሊረጋገጥ የሚችለው፤ የውስጥ ችግሮቻችንን ትርጉም ባለው መልኩ ለመፍታት የሚያስችል ህብረብሔራዊ የፌደራሊዝም ስርዓት ሲኖረን ነው የሚል ሲሆን፤እንዲሁም ደግሞ የሌሎች ሀገራት መንግስታትን አጉል ስጋት በወለደው የባላንጣነት ስሜት ከማየት ይልቅ ተቀራርቦ መነጋገርና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ ጤናማ ግንኙነትን ማስቀደም ይመረጣል የሚለው መርህ እንደ ሁለተኛ ቁልፍ ነጥብ ሊወሰድ ይችላል። እንግዲያውስ እንደኔ መረዳት ከሆነ ኢህአዴግ መራሹን መንግስት <<ለምዕራቡም ይሁን ለምስራቁ ዓለም ሀገራት ርዕዮተ ዓለማዊ እሳቤ የተለየ ጠብም - ፍቅርም እንዳይኖረውና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችን ሁሉ ለኢትዮጵያውያን የብሄር ብሔረሰብ ህዝቦች የፀረ ድህነት ትግል መጠናከር በሚኖረው ፋይዳ ብቻ የሚወሰን ተደርጎ የሚወሰድበት ምክንያትም ከተጠቆሙት ሁለት መሰረታዊ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን መለያ ህሪያት የሚመነጭ ግልፅ መርህ ስለሚከተል እንጂ እንዲያው ለይስሙላ ያህል የሚነገር አይደለም ባይ ነኝ። ይህን ስልም ደግሞ፤መላው የሀገራችን ህዝቦች ለብሔራዊ ማንነታቸው ተገቢ ዕውቅና የሚሰጥና ራስን በራስ የማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ መብት የሚረጋገጥበት ሕገ መንግስታዊ ስርዓት መመስረት አለበት የሚል ጥያቄ እያነሱ በተለያየ አግባብ ሲታገሉ የመኖራቸውን ያህል፤ የጥያቄያቸው የማያሻማ ምላሽ ማግኘቱን ተከትሎ የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ስር የሰደደ የድህነትና የሁዋላቀርነት ድቅድቅ ጨለማ አምርሮ ስለመታገል አስፈላጊነት ጉዳይ ማሰብ የማይጀምሩበት ምንም ዓይነት ሌላ አሳማኝ ምክንያት አለመኖሩን ለመረዳት ፖለቲከኛ መሆን አያስፈልገውም ማለቴ ነው።

ለዚህ የመከራከሪያ ነጥብ የተሻለ አብነት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል የምለው፤ የፌደራላዊት፤ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ህዝቦች የፀረ ድህነት ትግል ታሪክ ሂደት ዓይነተኛ መገለጫም፤ ሀገራችን በዓባይ ወንዝ ላይ ለምትገነባው ለታላቁ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ ስኬት ህብረተሰባችን የሚሰጠው ሁለንተናዊ ድጋፍ ተጠናክሮ ሲቀጥል የሚስተዋልበት ጉዳይ

ነው። ይልቁንም ደግሞ፤ የግድቡ ግንባታ በግብፅ ህዝብ ህልውና ላይ አሳሳቢ አደጋ የሚያስከትል አስመስለው ከማውራትና ከማስወራት ተቆጥበው የማያውቁት አንዳንድ የካይሮ ፖለቲከኞች፤ ኢትዮጵያን በህዝቦቿ የዕርስ በርስ ግጭት አተራምሰው ወደ ትናንቱ የጦርነት አዙሪት እንድትመለስ ለማድረግ ሲሉ የማይፈነቅሉት የከፋትና የጥፋት ድንጋይ አለመኖሩን ግምት ውስጥ አስገብተን ህብረተሰባችን ለግድቡ ግንባታ ዳር መድረስ የገባውን ቃል በማክበር ረገድ እያሳየ ያለውን ተሳትፎ ስንመለከተው ጉዳዩ ይበልጥ ጎልቶ ሊገለፅልን የሚችል ይመስለኛል። ከዚህ አኳያ ግብፆች አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥረው የግድቡን ግንባታ ሂደት ለማጓተትና ብሎም ለማስቆም ያለመ ጥረት ሲያደርጉ የሚስተዋሉበትን ስውር እንቅስቃሴ ከፕሬዚዳንት መህመድ ሙርሲ ለወራት ዕድሜ ብቻ የቆየ ያቺን ሀገር የመምራት ስልጣን ጀምሮ፤እርሳቸውን ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አይቶ እንዳላየ ባለፈው መፈንቅለ መንግስት አስወግደው የፕሬዘዳንትነቱን መንበረ ስልጣን እስከተረከቡት የአሁኑ ተረኛ አብዱል ፈታህ ዓልሲሲ ድረስ፤ እንዴት ባለ ተመሳሳይ ቅኝት ሲፈፀም እንደቆየ ለማየት ብንሞክር በእርግጥም የካይሮ መንግስታት እንደማይተኙልን የሚያመለክት ግብረ መልስ እናገኛለን።

ደግሞስ ግብፃውያኑ መንግስታት ከጥንት እስከ ዛሬ በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ የሚታወቁበት ተመሳሳይ የፖለቲካ ባህል ተደርጎ የሚወሰደው፤ በተለይም የዓባይ ተፋሰስን ጉዳይ በሚመለከት ማንኛውም ወደ ፕሬዝዳንታዊ መንበረ ስልጣኑ የመምጣት ዕድል የገጠመው የካይሮ ፖለቲከኛ ቢሆን፤ የተለየ አቋም የሚያሳይ መሆኑ አይደለም እንዴ? ለማንኛውም ግን የቀደሙትን የዚያች አገር መሪዎች ትተን፤ ከሆስኒ ሙባረክ በኋላ ወደ ፕሬዘዳንታዊው መንበረ ስልጣን የመምጣት ዕድል የገጠማቸው የአንድ ሰሞኑ መሃመድ ሙርሲና እንዲሁም ደግሞ አሁንም ድረስ በካይሮው ቤተመንግስት ውስጥ የሚገኙት አብዱልፈታህዓል ሲሲ፤ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ የውሃ ሀብቷ እንዳትጠቀም ለማድረግ ሲሉ ያሳዩትን ተመሳሳይ ሊባል የሚችል የእክል ፈጠራ እንቅስቃሴ ብቻ እንኳን ብንመለከት፤ ስለ ግብፅ ፖለቲከኞች ግትር አቋም የተሻለ ግንዛቤ መጨበጥ የሚቻል ይመስለኛል። ስለሆነም ኢትዮጵያና ግብፅ ከሙርሲ እስከ ዓልሲሲ ባለው የቅርብ ጊዜ ግንኙነታቸው የዓባይ ተፋሰስን ጉዳይ አስመልክተው ሲያሳዩ ስለቆዩት አቋም ለማስታወስ ያህል አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት ተገቢነት ይኖረዋል ብየ አምናለሁ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተንደረደርኩበትን መሰረተ ሃሳብ መነሻ አድርገን፤የኢትዮጵያና የግብፅ መንግስታት የውሃ ፖለቲካ የወለደው ዲፕሎማሲያዊ ትንቅንቅ አሁን የደረሰበትን የመካረር አዝማሚያ ሊያስከትል ስለቻለባቸው ተጨባጭ ምክንያቶች እንነጋገር ከተባለ፤ ለውጥረቱ መፈጠርም ሆነ እየተባባሰ መምጣት እንደ ዋነኛ መንስኤ ሊወሰድ የሚችለው ቁልፍ ነጥብ፣ የካይሮ ፖለቲከኞች ጉዳዩን አምነው ለመቀበል አለመፈለጋቸው ነው ማለት ይቻላል። ይህን አስተያየቴን ለራስ ሀገር ከማድላት የሚመነጭ የአንድ ወገን አቋም አድርጎ የሚገምት አንባቢ ካለም፤ በተለይ አብዛኛዎቹ የካይሮ መገናኛ ብዙሃን አዘውትረው ሲዘግቡት የቆዩትን ስለ የህዳሴው ግድብ የግንባታ ሂደት የሚያወሳ ተከታታይ አሉታዊ ዜና ያስታውስ ዘንድ እመክረዋለሁ። ምክንያቱ ደግሞ እነዚሁ የግብፅ ሚዲያዎች በየወቅቱ ከህዳሴው ግድብ የግንባታ ሂደት ጋር አያያዙ የሚዘግቧቸው ዜናዎች ቅኝት የሚያረጋግጥልን ጥሬ ሀቅ ቢኖር፤ የአክራሪው

“ሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ” መሪ መሐመድ ሙርሲና አብዱልፈታህዓል ሲሲ ጉዳዩን የሚያዩበት መነፅር ፍፁም ተመሳሳይ እንደሆነ አጎልቶ የሚያንፀባርቅ እውነታ መኖሩንም ጭምር ነው ብንል ከተጨባጩ ጥሬ ሀቅ የሚያርቀን እንዳልሆነ ይሰማኛልና ነው።

ከዚህ የተነሳም፤ ኢትዮጵያ፤ ግብፅና ሱዳን የግድቡ ግንባታ በታችኞቹ የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት ላይ የጎላ ስጋት ሊያሳድር የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን እየገመገሙ የጋራ ግንዛቤ ለመጨበጥና እንዲሁም ቀጣናዊ መተማመንን ለመፍጠር ሲሉ፤ ለዓመታት ያካሄዱትን የሶስትዮሽ ምክክር መድረክ ምንም ዓይነት ጠቃሚ ውጤት ያመጣል ተብሎ የማይጠበቅ ረብ  የለሽ ነገር እንደሆነ አድርገው በመዘገብ የሚታወቁት የካይሮ ሚዲያዎች ቁጥር ጥቂት አይደለም። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ መንግስት የግብፅ መገናኛ ብዙኃን የህዳሴው ግድብን አስመልክተው የሚያሰራጩት አፍራሽ መረጃ፤ ሀገራቸው በሶስትዮሽ የምክክር መድረክ ላይ የተስማማችበትን የፍትሐዊ  ተጠቃሚነት መርሆ የሚጥስ ድርጊት መሆኑን ከመግለፅና ይህን ያልተገባ ድርጊታቸውን እንዲያቆሙ ከመጠየቅ የተቆጠበበት አጋጣሚ ባይኖርም፤ እነርሱ ግን ነገር ማጋጋላቸውን የማቆም አዝማሚያ አይታይባቸውም።

ይልቁንም አሁን በሽብር ወንጀል ተከሰውና እስከ የሞት ፍርድ ሊደርስ እንደሚችል የጥፋተኝነት ብይን ተላልፎባቸውም ጭምር በፅኑ እስር ላይ እንደሚገኙ የሚነገርላቸው የአንድ ሰሞኑ ፕሬዚዳንት መሐመድ ሙርሲ፤ በስልጣናቸው  የመጨረሻ ቀናት ውስጥ “የዓባይ ወንዝ ውሃ ለግብፅ ህዝብ የህልውና ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ኢትዮጵያ የጀመረቹውን የግድብ ግንባታ እንድታቆም እንጠይቃለን። የኢትዮጵያው መንግስት ይህን ማሳሰቢያ ካልተቀበለም ደግሞ የጦርሃይላችንን አስተማማኝ ወታደራዊ አቅም ተጠቅመን የህዳሴ ግድብ የሚሉትን ግንባታ እንዲያቆሙ ለማድረግ እንገደዳለን!” ሲሉ የተደመጡበትን ይፋዊ ዛቻ ተግባር ላይ ስለማዋል አስፈላጊነት ለተተኪው የዚያች ሀገር መሪ፤ ለፕሬዘዳንት አብዱልፈታህ ዓልሲሲ አስተዳደር የማስገንዘብ ቅኝት የተከተለ የጠብ አጫሪነት ይዘት ባለው ዘገባ ነገሩን ለማጋጋል ያለመ ብርቱ ጥረት ማድረግን ነው የካይሮ ሚዲያዎች የመረጡት። እናም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፕሬዚዳንት ዓልሲሲ መንግስት እያሳየ ያለውን፤ የመሐመድ ሙርሲን ይፋዊ ዛቻ የመድገም አዝማሚያ ለታዘበ ሰው ግብፃውያኑ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች እስከ ዛሬ ድረስ አበክረው ሲወተዉቱ  የቆዩበት ነገር የማጋጋል “ጥረት” እየሰመረላቸው ይሆን እንዴ? ብሎ ራሱን መጠየቁ አይቀርም።

እንዴት ብትሉኝም ደግሞ፤ ከዋነኞቹ የዓባይ ተፋሰስ ባለድርሻ ሀገራት መካከል የሚመደቡት ኢትዮጵያና ግብፅ በታላቁ የህዳሴ ሃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ ምክንያት፤ ከመሐመድ ሙርሲ እስከ አብዱልፈታህ ዓልሲሲ የፕሬዘዳንት ስልጣን ዘመን ድረስ የዘለቀ ዲፕሎማሲያዊ ፍጥጫ ያስተናገዱበት የውሃ ፖለቲካ እሰጥአገባ አሁን አሁን ወደለየለት ትንቅንቅ እያመራ ስለመምጣቱ ዓለም አቀፋዊ የመረጃ ምንጮች ጭምር ያመለክታሉና ነው። ለአብነት ያህልም የግብፅ ፕሬዚንዳንት አብዱልፈታህ ዓልሲሲ  ራሳቸው በቅርቡ አንድ ሰው ሰራሽ የዓሳ ማራቢያ ሐይቅን መርቀው ሲከፍቱ የመሐመድ ሙርሲን ኢትዮጵያን ለማስፈራራት ያለመ ዛቻ ቃል በቃል የደገሙበትን ጠብ አጫሪ ንግግር አሰምተዋል

ሲሉ የታመኑ ምንጮች ዘግበዋል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ፕሬዝዳንቱ ሰሞኑን ወደሪያድ አቅንተው ለሳዑዲ ዓረቢያው ንጉሳዊ መንግስት "ኢትዮጵያ የግብፅ ህዝብ ህልውና የተመሰረተበትን የዓባይ ወንዝ ውሀ ገድባ ተስፋችንን ሁሉ ልታጨልመው ቆርጣ መነሳቷን እያያችሁ ዝም ትላላችሁ እንዴ? ·ረ በአላህ ያቺ ድህነት የደቆሳት ሀገር መገንባት የያዘቺውን የህዳሴ ግድብ ለማቆም እንድትገደድ የሚያደርግ ተፅእኖ በመፍጠር ረገድ ድጋፋችሁን እንሻለንና አትንፈጉን!?"ሲሉ መማፀናቸውንም ጭምር ነው የመረጃ ምንጮቹ አክለው የገለፁት፡፡ የሪያዱ ንጉሳዊ ስርዓት "ሳዑዲ ዓረቢያ መቸም ቢሆን ለግብፅ ብሔራዊ ጥቅም መረጋገጥ ከጎናችሁ ትቆማለች" የሚል ምላሽ እንደሰጣቸውም ሚዲያዎች ዘግበዋል፡፡

እንዲሁም የግብፅ መንግስት ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻውን ለአሜሪካና ለሌሎች ምዕራባውያን ለጋሽ ሀገራት የማዳረስ ጥረት በማድረግ ላይ ስለመሆኑ ነው ረቡዕ ህዳር 13 ቀን ታትሞ የወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ የዘገበው፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ፤ ግብፅ እና ሱዳን የህዳሴው ግድብ የሚገነባበትን አግባብ አስመልክተው ሲያካሂዱ የቆዩት ምክክር እንዳልተሳካና ከዚህ በኋላ ሌላ አማራጭ መፍትሔ ወደመፈለግ ፊታቸውን እንዳዞሩ አድርገው የማስረዳት ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ጀምረዋል ነው የሚባለው ግብፆች፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የካይሮ ሚዲያዎች አሁንም ድረስ እያንዳንዷን የኢትዮጵያ መንግስት ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እየተከታተሉ ከህዳሴው ግድብ የግንባታ ሂደት ጋር የሚያያዝ ትርጉም የመስጠት ፀጉር ስንጠቃቸውን እንደቀጠሉ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሰሞኑ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጠው ወቅታዊ ማብራሪያ አስታውቋል፡፡

በዚህ መሰረትም ጠቅላይ ሚኒስትር ሃ/ማርያም ደሳለኝ ወደ ኳታር የሄዱት ለህዳሴው ግድብ ግንባታ የሚውል የገንዘብ ዕርዳታ ለመጠየቅ እንደነበረና እንደቀናቸውም ጭምር ጠቅሰው የዘገቡ የግብፅ ሚዲያዎች መኖራቸውን ነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባዩ አቶ መለስ ዓለም በሰሞነኛ ጋዜጣዊ መግለጫቸው ላይ ያመለከቱት፡፡ የግብፅ መገናኛ ብዙኃን የኳታር መንግስት ለህዳሴው ግድብ ግንባታ የሚውል ገንዘብ ለኢትዮጵያ ረድቷታል ሲሉ መዘገባቸው ከእውነት የራቀ ስለመሆኑ ሲያስረዱም አቶ መለስ ዓለም "ግድቡ የሀገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች በራስ አቅም ብቻ የሚገነቡት እንጂ የማንኛውንም የውጭ መንግስት ዕርዳታ የምንጠይቅበት አይደለም፡፡ ለታላቁ የህዳሴው ግድባችን ግንባታ የሚያስፈልገንን የፋይናንስ ወጭ የሚሸፍነው የኢትዮጵያ ህዝብ ራሱ እንደሆነ ዓለም አቀፍ ማህበረሰብም ጭምር ያውቃል" ነው ያሉት፡፡ እንዲያውም "የግድቡ ግንባታ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የገንዘብ ምንጮቹም መሃንዲሶቹም እኛው ራሳችን ነን" ሲሉ የቀድሞው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ለግድቡ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ የተናገሩትን የሚያስታውስ ሃሳብ ሰንዝረዋል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ጽ/ቤት ሃላፊው፡፡

ስለዚህም የግብፅ መንግስት ሀገራችን ስሚኒያ አምስት ከመቶ ያህል የውሃ ድርሻ በምታወጣበት የዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባች ያለውን ታላቁን የህዳሴ ሃይል ማመንጫ ግድብ ወደ ማገባደድ እየተቃረበች ስለመሆኗ በሚነገርበት በአሁኑ ወቅት፤ የማይጠበቅ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ማሳየት መጀመሩ ሊያስገርም

ቢችልም ግን ደግሞ እውነት ነው፡፡ በፕሬዘዳንት አብዱል ፈታህ ዓልሲሲ የሚመራው የካይሮ አስተዳደር እዚህ ውሳኔ መድረስን የመረጠውም፤ ሰሞኑን ራሷው ግብፅ ባስተናገደቺው፤ የምስራቅ ናይል ተፋሰስ አባል ሀገራት እየተባሉ የሚጠሩት ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን ለ17ኛ ጊዜ ባካሄዱት ሰብሰባ ላይ፤ የቅኝ ግዛት ዘመኑ ስምምነት እንዲፀና ጠይቆ ጥያቄውን ሁለቱ ሀገራት ውድቅ ስላደረጉት ነው ተብሏል፡፡ ወጣም ወረደም ግን፤ ኢትዮጵያ የዓባይ ወንዝ መነሻ ሀገር እንደመሆኗ መጠን አንጡራ የውሃ ሀብቷን ለተያያዘቺው የፀረ ድህነት ትግል በሚጠቅም የልማት ተግባር ላይ እንዳታውል ሊያግዳት የሚችል ምንም ዓይነት ምክንያት ይኖራል ተብሎ አይታመንም፡፡ ምንም እንኳን የግብፅ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያን በህዝቦቿ ብጥብጥ ለማተራመስ ያለመ ሴራቸውን ቀጥለው በውስጥ ጉዳያችን ከመግባት እንቅስቃሴ ይቆጠባሉ ተብሎ ባይጠበቅም፤ ግን ደግሞ <<አተርፍ ባይ አጉዳይ>> ከመሆን ያለፈ ውጤት ሊያመጡ እንደማይችሉ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በተረፈ እኔ ለዛሬው እዚህ ላይ አብቅቻለሁ፡፡ መዓሰላማት